# ፖለቲካ ጥገኝነት ለሚጠይቁትና ጥገኝነት ለተሰጣቸው የሚመለከቱ የጤና መረጃዎች

Co-funded by the Asylum, Migration and Integration Fund of the European Union

SISTEMA SANITARIO REGIONALE ASL ROMA 1

REGIONE LAZIO

Progetto ICARE

*Integration and Community Care*

*for Asylum and Refugees in Emergency*

HOME/2017/AMIF/AG/AMAS/0075

CUP E89FI8001260006

*Responsabile Regione Lazio*
*Giancarlo Santone*

SISTEMA SANITARIO REGIONALE
ASL ROMA 1

REGIONE LAZIO

ተገደው ለስደትለተጋለጡት
ዜጎች የቆመ የጤና ማእከል

በ Asl Roma 1 የሚገኘው የጤና ማእከል ተገደው ለስደት ለተጋለጡት ዜጋዎች ብሎ የቆመ የጤና ማእከል ሆኖ ኣላማው በማህበራዊና ጤናን በተመለከተ ጉዳይ ኣጥጋቢ የሆነውን መልስ ለመስጠት ነው።

ይህን የተጠቀሰ ኣገልግሎት በመጀመርያ የጦርነት ግዳይ ለሆኑትን፣ ኣካላዊ ስቃይ ወይም ግፍ ለደረሰባቸዉ፣ ሆን ብሎ ለሚፈጸሙት በደላቶች(ፖለቲካዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ጾታዊ፣ የግዳጅ ወሲብ፣ ወዘተ)ለተጋለጡ፣ ወሲባዊ በደል፣ግርዛት (MGF) ለመሳሰሉት ይከታተላል።

በተጨማሪም ይህን ማእከል በቸንትሮ ኣስታሊ፣ በሮማ ከተማ ኣስተዳደር እንደዚሁም ከተለያዩትን ፕሮጀክቶች በሚሸፈን ወጪ የተለያዩትን ቋንቋ የሚናገሩ ተርጓሚዎች ያቀርባል።

የዚህ ማእከል ኣላማ በጤና ጥበቃና በማህበራዊና ስራ ኣመካኘነት ለተለያዩት ባለሞያ ሃኪሞች ማቀራረብና በተሻለ መንገድ ኣብረው እንዲሰሩ ዘንድ የቆመ ነው።

የዚህ ማእከል ቀዋሚ ሰራተኞች የሚከተሉት ናቸው ። ሃኪሞች፣ የስነኣምሮ ባለሞያዎች፣ ነርሶች፣ የጽንስ ረዳት ሃኪሞች፣ ስለ ማህበራዊ ጉዳይ የሚከታተሉት ሰራተኞች፣ በቸንትሮ ኣስታሊ የሚያገለግሊሉ ስለ ፖለቲካ ጥገኝነት (ኣሳይለም)

የሚከታተሉ የህግ ባለሞያዎች  ናቸው።
ተመርቀው ትምህርታቸው የጨረሱት ተማሪዎች ችሎታቸው ለማበልጸግ በሞያውያን ሃኪሞች ታጅበው ኮርስ መከታተል ይችላሉ።
ይህ የጤና ማእከል ከሰኞ እስከ ኣርብ ከጠዋቱ 9,00  ሰዓት እስከ 5,00 ክፍት ነው።

የዚህ ማዕከል ኣገልግሎት እንደሚከተለው ነው

የማስተናገጃና የጤና ጥቆማ የሚሰጥበት ክፍል

የስብሰባና  የውይይት ክፍል

ቀዋሚ የሆነው የቋንቋ ትርጉም ኣገልግሎት
ኣማርኛ፣ ኣረብ፣ ባምባራ፣ ባንግላ፣ ቻይና፣ ኩርድሽ፣ ዳሪ፣ ጁላ፣ ፋርሲ፣ ፈረንሳይ፣ሂንዲ፣ እንግሊዘኛ፣ ማንዲንጋ፣ ፓሽቱ፣ ፒጂን፣ ፑላር፣ ሶማል፣ ሶኒንከ፣ ሶራኒ፣ ስፓንሽ፣ ትግርኛ፣ ኡርዱ፣ ዎሎፍ
ከዚህ ውጭ ለሆኑትን ቋይንቋዎች በስልክ ተደውሎ የትርጉም ኣገልግሎት መጠየቅ ይቻላል።

አጠቃላይ የሆነው ህክምና የሚሰጥበት ክፍል
የስነ ኣእምሮ ህክምና(ሳይክያትሪ)ክፍል
የስነ ኣእምሮ ህክምና(ሳይኮሎጂ)ክፍል
የህግ ኣዋቂ ሃኪም ክፍል
የማህጸን ህክምና ክፍል
የኣጥንት ህክምና(ኦርቶፐዲ)

ማህበራዊ ጉዳዮች የሚከታተል ኣገልግሎት

አጠቃላይ የሆነው ህክምናና የጥቆማ ኣገልግሎት ለማግኘት ያለቀጠሮ መቅረብ ይቻላል።
ወደ ባለሞያ ሃኪሞች ለመቅረብ ቀጠሮ ተይዞ መቅረብ ይቻላል።
ቢሆንም ኣስቸኳይ ለሆኑት ጉዳዮች ፈጣን መልስ ይሰጣል።

**የፖለቲካ ጥገኝነት  (  ኣሳይለም)**

## ጠያቂዎች ለሆኑትን ስለ

## ጤና የሚመለከትቱ ሂደቶች

### ስደተኞች በሚኖሩበት ሰፈር ወይም ካምፕ መከተል ያለበት የጽዳት ዘዴ

ከተላላፊ በሽታዎች ለመከላከል ተገቢ የሆኑትን የጽዳት ዘዴዎች መከተል ያስፈልጋል

### የኣካል ጽዳት

እጅ መታጠብ ዋናውና የመጀመርያ የኣካል ጽዳትን ሆኖ ይህን ልማድ ደግሞ

- ቆሻሻ ወይም የተበከለ እቃ ስያዝ
- ምግብ ሲቀቀል፣ ሲበላ ወይም ሲታደል
- መድሃኒት ክኒን ሲታደል፣ መርፍየ ሲወጋ

ጥፍር ዘውትር የተቆረጠ ቢሆን ይመረጣል።
ለእጅ ጽዳት መሰናክል ሊሆኑ የሚችሉትን እንደ ኣምበር፣ ቀለበት፣ ሰው ሰራሽ ጥፍሮች ኣለመልበስ ይመረጣል።

ውሃና ሳሙና በተለይም ጸረባክተርያ ሳሙና በመጠቀም እጅ ማጠብ ያስፈልጋል።
ለግማሽ ደቂቃ ያህል በተለይ በጣቶች መካከል ኣረፋ እስከሚወጣ ማሸት ይገባል።
ኣረፋው ነጭ እስካልሆነ ድረስ ሳሙና መጨመር ያስፈልጋል። ቆሻሻ ነገሮች ወይም ሽንትቤት ውስጥ የሚገኙትን እቃውች ሲጸዳ ጓንት መልበስ ያስፈልጋል።
የታመመ ወይም ኣሮጌዎች ሲንከባከቡ በየግዜው ጓንት መቀየር ያስፈልጋል።።

የግል ንብረታችን እንደ ኣፍንጨ መሃረብ፣ ፎጣ፣ ምላጭ፣ የጥርስ ብሩሽ፣ የጥፍር ማጽጫ ኣንዴ ተጠቅሞ የሚጣ ቢሆን ይሻላል፣
ኣለበለዝያ በጽዳት መያዝ ያስፈልጋል።
ልብስ፣ ፎጣ፣ አንሶላ ቢያንስ በሳምንት ኣንዴ መቀየር ያስፈልጋል።

### ለጤና ዋስትና የሚያገለግሉ መሳርያዎች DPI

ስደተኞች በሚኖሩበት ሰፈሮች ወይም ካምፕ ለጤና ዋስትና የሚያገለግሉ መሳርያዎች ጓንትና የኣፍንጨ ሽፋን ኣስፈላጊ ናቸው። የነዚህ መሳርያ ዋስትና ወደካምፕ ከሚገቡት

ኣዲስ እንግዳዎች ብቻ ሳይሆን ለራሳቸው ዋስትናም ነዉ።
መጠለያ ካምፕ ውስጥና ኣደገኛ ቦታ ውስጥ ለሚሰሩትን ይህን መሳርያ መጠቀም ያስፈልጋል ሆኖም ኣስፈላጊነት በሌለበት ግዜ መልበስ ኣያስፈልግም።
ጉንፋን ከታመመ ሰው ንግግር ሲካሄድ ከሳልና ከማስነጠስ የኣፍንጨው ሽፋን ሊከላከልልን ይችላል። የቆዳ ችግር ወይም በቆዳቸው ያልዳነ ቁስል ያለባቸው ሰዎች ስንነካ ጓንት መልበስ ኣስፈላጊ ነው።

## ለጤና ዋስትና የሚያገለግሉ መሳርያዎች

ሁለት ኣይነት የኣፍንጨ ሽፋን ኣለ

- ቀዶ ጥገና የሚያደርጉት ሃኪሞች የሚለብሱት

ይህን ኣይነት መከላከያ ወደ ህመምተኛ ባክቴሪያዎች እንዳይሽጋገሩ የሚከላከል ነው። ብያንስ በየስምንት ሳኣት መቀየር ያለበት መካላከያ ሆኖ ሲበላሽ ወይም እርጥብ ሲሆን መለወጥ ያስፈልጋል።

- ከባድ በሽታ ከታመሙት ጋር ሲሰራ የሚለበስ የኣፍንጫ ሽፋን

እንደ ሳንባ ነቀርሳ፣ ማጅራት ገትር የመሳሰሉትን በሽታዎች በሚታከሙበት ስፍራዎች የሚለበስ የኣፍንጫ ሽፋን ሆኖ በየሁለት ሳኣት መቀየር ይገባል።
ሃምሌ 15 2003 የታወጀው ቁ 388 ኣንቀጽ 46 81/2008 ስለ የመጀመሪያ እርዳታ ሳጥን ኣጠቃቀም መምርያ ይሰጣል።

## የኣከባቢ ጽዳድ

- ኣከባብያችን በተቻለ መጠን ከማያስፈልጉትና ከተጣሉት መሳሪያዎች ነጻ መሆን ኣለበት
- በተቻለ መጠን ኣደጋ እንዲከሰት ከሚጋብዙት ነገሮች መጠንቀቅ። ስለታም ወይም የሚወጉ ነገሮች በጥንቃቄ መጠቀም ያስፈልጋል
- ኣንድ ኣልጋ ከሌላው ብያንስ የ 70 ሰንቲሜትር ርቀት እንዲኖረውና ኣየር ከሚነፍስበትና ሃይለኛ የሙቅት ምንጭ ከሚመጣበት መራቅ ይኖርበታል
- በሮችና መስኮቶች በደምብ መዘጋታቸው ማረጋገጥ

| የጽዳት ግዜ | መጽዳት ያለበት ቦታ ወይም ነገር | የማጽጃ ዓይነት (ኬሚካል) |
|---|---|---|

| | | |
|---|---|---|
| ከመጠቀም በሃላ | የምግብ መገልገያዎች (ሳህን-ማንክያ- ቢላ ወዘተ)<br>የመጥበሻ እቃዎች (ድስት-ምግብ ማብሰያ ወዘተ)<br>የምግብ ገበታ- ጠረጴዛ | ሳሙና ጸረ-ባክቴሪያ |
| በየቀኑ (ጠዋት- ከሰዓት በሃላ - ከእራት በሃላ | ሽንትቤትና እዛ ውስጥ የሚገኙት እቃዎች መልካም በሆነው ሁኔታ መጽዳት ኣለበት | ሳሙና ጸረ-ባክቴሪያ |
| አስፈላጊ ከሆነ / በየቀኑ | • ሽንትቤትና እዛ ውስጥ የሚገኙት እቃዎች ከነውሃ ቧንቧና ተመሳሳይ<br>• የማብሰያ ክፍል፣ የመመገቢያ ክፍል፣ የምግብ ገበታ-ጠረጴዛ ፣ምድጃ፣ ድስት የሚታጠብበት ገንዳ፣ የማብሰያ ክፍል ወለል<br>• የመኝታ ክፍሎች ወለል<br>• ሰንጠረዦች | ሳሙና ጸረ-ባክቴሪያ |
| በየሳምንቱ | ሰንጠረዥ፣ ወምበሮች፣ የበር መክፈቻ መያዣ | ሳሙና ጸረ-ባክቴሪያ |
| በየወሩ | መስታወት፣ ቁም ሳጥን፣ በር | ጸረ-ባክቴሪያ |

**ግርዛት የደረሰባቸው ሴቶች የመለየት ሂደት MGF** በሚል አህጽሮተ ቃል ይታወቃል። ይህ ማለት በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የተገረዙት ሴቶች ለመለየት የሚሰጥ ቃል ነው። ስደተኞች በሚኖሩበት መጠለያ ካምፕ ውስጥ የሚሰሩት ኣባላቶች ይህን የግርዛት ጉዳይ በደምብ ኣውቀው ዝግጁ መሆንም ይኖርባቸዋል። በተጨማሪም ሴቶቹይን የመጡበት ሃገር ለይተው ኣውቀው መሰላቸውን ስለሚመለከት ተገቢ መረጃ

መስጠት ይኖርባቻዋል። ስለዚህ ጉዳይ ለመነጋገር ሴትዋን ተመቻችታና ተረጋግታ በሚመች ክፍል ቁጭ ኣርገህ ማወያየት ይገባል። የትም ዓይነት ፍርድ ወይም ውንጀላ ም አጠት ኣይገባም።

**የኣንጀት ተውሳክ ወይም ፓራሳይት**

ይህንይ ኣይነት በሽታ በውሃ ውስጥ ወይም መሬት ላይ በሚገኝ ባክተርያ ይመጣል። በኣንዳንድ ታዳጊ ኣገሮች ይህን በሽታ በጣም ኣደገኛ ነው። ከፍተኛ ሙቀት ባለበት ስፍራ፣ ከሰሃራ በታች የሚገኙት የኣፍሪካ ሃገሮች፣ ላቲን ኣመሪካ፣ ቻይናና ምስራቅ እስያ በብዛት ይታያል።
ኣንዳንድ ኣደገኛ እንደ ስኪስቶሶማ (schistosomiasi) ወይም ብልሃርዝያ (bilharziosi) ስትሮንጂሎይድ(strongyloidosi) የተባሉትን በሽታዎች ለረጅም ኣመታት ኣካል ውስጥ ተቀፍቅፈው ይቆዩና ወደ ምት ልያደርሱ ይችላሉ።

**በግብጽ ብልሃያርዝያ በብዛት ይታያል**

የኣንጀት ተውሳክ ወይም ፓራሳይት በሚታይበት ግዜ ሃኪሞች የሚገባውን ጥያቄ በማቅረብ የታካሚውን የድሮ የጤና መረጃዎችን ማወቅ ይገባቸዋል ። በተለይ ተቅማት፣ ማስመለስ፣ ማስታወክ፣ የሆድ ህመም፣ ለረጅም ግዜ የሚቆይ ማሳከክ፣ በፊንጢጣና ኣከባቢው ማሳከክ፣ በሽንት ደም ሲታይ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል።
የደም ምርመራ በሚደረግበት ግዜ ነጭ የደም ሕዋሳትና ብዛታቸው ከጨመረ ሆኖም ግን ምንም መጥፎ ስሜት ባይሰማም ለማንኛውም ሃኪም ይህን የሚከተለውን ምርመራ ማዘዝ ይገባዋል።

- የተባዮች ወይም የፓራሳይት መኖር የምያሳይ ምርመራ
- ጸረ ስኪስቶሶማ (Ab anti schistosoma) ምርመራ

የዚህ ምርመራ ውጥየት በሽታው ኣንዳለ ካሳየ ባስቸኳይ ተገቢው ህክምና ማድረግ ይገባል።

**ስካብያ scabbia የቆዳ በሽታ**

ይህ የቆዳ በሽታ ቆዳ ውስጥ በሚገባ ተባይ ወይም ፓራሳይት የሚመጣ ሆኖ ስካብያ መሆኑን የምናውቀው ቆዳ ሲነፋት ወይም ውሃ የያዘ እብጠት ሲከሰት ነው። ። ይህን ኣይነት ህማም በተለይ ለሊት ሲሆን በጣም ያሳክካል። ምልክቶቹን በመላ ኣካል ቢታዩም በተለይ በጩኖች መካከል፣ በብብት፣ በእጅና በጣቶች መካከል ይበዛል።

**የበሽታው እድሜ**

ስካብያ ታሞ በማያውቅ ሰው ክሁለት ሳምንት እስከ ስድስት ሳምንት ይቆያል

**ስካብያ የሚተላለፍበት መንገድ**

የዚህ ተባይ እንቁላል እስካልሞቱ ድረስ በሽታው በሰውነት ይቆያል። ተገቢው ህክምና ተደርጎ ገና በሽታው ካልጠፋ ከኣንድ ሳምንት በሃላ መድሃኒቱን መድገም ያስፈልጋል።

**በሽታውን የማሰተላለፍ ችሎታ**

ያልታመመ ሰው ከታመመ ሰው ጋር ለረጅም ግዜ ሲቀርብ፣ ኣንድ ላይ ሲኖር ወይም ሲነካ በሽታው ይዘዋወራል። ኣንዳንድ ግዜ የታመመውን የለበሰው ወይ የበከለው ልብስ፣ ኣንሶላ፣ ፎጣ በሽታው ማስተላለፍ ይችላሉ።

**ስካብያ የታመመ ሰው ማድረግ ያለበት ጥንቃቄ**

በመጀመርያ በሽተኛው ለብቻው ሊሆንና ወደሚመለከተው የህክምና ቦታ መሄድ ኣለበት። ቀጥሎ ተገቢው የሆነው ጸረ ስካብያ መድሃኒት መጠቀም ኣለበት።

**መድሃኒት**

ሃኪም እንዳዘዘው መሰረት ተገቢውን መድሃኒት መጠቀም። መድሃኒት ቤት የተለያዩትን ቅባት በተለይ permetrina 5% የተባለ ወይም benzoato di benzile 10% ወይም 20% በመጠቀም የተሻለውን ውጤት ማግኘት ይቻላል።
በሽተኛው ያስታመሙት ወይም ከሱ ጋር በቅርብ የኖሩትን ልክ በሽተኛው እንዳደረገው መድያኒቱን መጠቀም ይገባቸዋል። ኣንሶላ፣ የኣልጋ ምንጣፍ፣ የኣልጋ ትራስ፣ በማጠብያ ማሽን በ 60 ዲግሪ ማጠብ ይገባል። በሙቅ ውሃ መታጠብ የማይችሉት ነገሮች በፕላስቲክ ቀረጢት ታሽገው ለኣንድ ሳምንት ቁጭ ማድረግ ይገባል።

**ቅማል**

ቅማል ጸጉር ላይ ተደብቆ የሚኖር ተባይ ወይም ፓራሳይት ሆኖ ደም እየመጠጠ ይኖራል። የቅማል እንቁላል (0,3- 0,8) ርዝመት ኖሮት ከ 6- 8 ቀናት በሃላ እንቁላሉን ወደ ቅማል ይቀየራል።
ከጸጉር ውጭ የቅማል እድሜ ከ 24- 48 ሰዓት ኣያልፍም። በተጨማሪም ከሰዉነታችን ሙቀት በታች የሆነውን ሙቀት በሚኖርበት ግዜ እንቁላሉን ወደ ቅማል መቀየር ኣይችልም።
በኣለም ላይ በሚልዮን የሚቆጠሩት ሰዎች የቅማል ተጠቂ ሊሆኑ ይችላሉ። የኡሮ

መጠን፣ የጸጉር ርዝመት ወይ ንጽህና አለመጠበቅ ከቅማል መስፋፋት ግንኙነት የለውም።
ቅማል ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፍበት ራስ ከራስ ሲገናኝ ወይም በኮፍያ፣ ማበጠሪያ፣ ያንገት ሻሽ ወዘተ አመካኝነት ነው።
የቅማል ተባይ ወይም ፓራሳይት አደገኛ ህመም ባለመሆኑ በሰው ሂወት ላይ አደጋ አያስከትልም።

**መድሃሊት**
ሃኪም እንዳዘዘው መሰረት በበድሃኒት መሸጫ ቤት የተለያዩትን ቅባት ወይም ሻምፖ ይገኛሉ።

**አከባቢና ንብረቶች በጽዳት መያዝ**
ለሁለት ቀል የለበስነው ልብስ፣ ፎጣ፣ አንሶላ ወዘተ በማጠብያ ማሽን በ 60 ዲግሪ ማጠብ።
በሙቅ ውሃ መታጠብ የማይችሉት ነገሮች (አልጋ ምንጣፍ፣ ኮፍያ፣ የአንገት ሻስ፣ ሹራብ)በልብስ መጥረግያ ማጽዳት ወይም ለ 48 ሰዓት በፕላስቲክ ከረጢት መዝጋት ይገባል። ማበጠርያ በጣም ሙቅ በሆነ ውሃና ሳሙና ማጠብ ያስፈልጋል።
በኤለትሪክ መጥረግያ የመሬት ምንጣፍና ሶፋ ማጽዳት።

**ለጉበት በሽታና (ሂፓታይት) ለኤች አይ ቪ HIV የሚመለከቱ መረጃዎች**

**ሂታታይት ኤ- A**

ይህን በሽታ ጉበት የምያጠቃ በሽታ ሆኖ የሚተላለፍበት በአፍ፣ ሰገራ፣ የተበከለ ውሃና ምግብ፣ ለረጅም ግዜ ከብዙ ሰው ጋር ጽዳት በሌለበት ቦታ ሲቀመጥ፣ የግል ንጽህና በሚገባ በማይከተልበት ግዜ ሊነሳ ይችላል። ሰገራ ከተወጣ በሃላ ቫይረሱን ከሱ ስለሚወጣ ሽንትቤት ከተሄደ ቦሃላ እጅ በደምብ ማጠብ ያስፈልጋል
በሰውነት ውስጥ ይህን በሽታ ክ 15 እስከ 50 ቀን መቆየት ይችላል። የዚህ በሽታ ምልክቶች ደግሞ ድካም፣ ትኩሳት፣ የምግብ ፍላጎት ማጣት፣ ማስታወክ፣ ማስመለስ፣ የሆድ ህመም ሆኖ ከተዘረዘሩትን ጭምር ብጫ ሽንት፣ ወደ ነጭ ቀለም የሚሄድ የሰገራ ቀለም፣ ብጫ ወዝና የአይን ቀለም ሲታይ ጥርጣሬ ማሳደር ይገባል።

**ሂፓታይት ቢ- B**

ይህን በሽታ በማንኛውም ሁኔታና ወቅት ሊታይ ይችላል። ከተበከለ ደም ጋር ቅርበት

ሲደረግ (ደም መለገስ፣ መርፍየ መውጋት፣ ከተባይ ያልመከነ የህክምና መሳርያ፣ ምላጭ፣ የጥርስ ብራሽ፣ መቀስ ወዘተ) በሽታው ይነሳል። በተጨማሪም ያለመከላከያ ወሲብ ሲፈጸም ክእናት ወደ ልጅ በጡት ወተት ሊሸጋገር ይችላል።
ኣካል ውስጥ ከ 45 እስከ 180 ቀን ሊቆኢ ይችላል ሆኖም ግን ብቅ ማለት የሚችለው ከ 60/90 ቀን ነው።
ይህን ዓይነት በሽታ በግዜ ህክምና ካላገኘ ወደ ጉበት ካንሰር  ወይም cirrosi epatica መለወጥ ይችላል።
 ሂፓታይት ቢ- B ልያጠቃቸው የሚችል ወይም የተጋለጡትን የበስተኛው ቤተሰብ፣ የጭስ ሱሰኞች በምያደርጉት የመርፍየ መለዋዋጥ፣ የሚወቀሩት፣ ባልመከነ የህክምና መሳርያ ቀዶ ጥገናና ወይም ጥርስ የምያስነቅሉ ወዘተ ናቸው።
ከዚ ሁሉ ለመከላከል የግል ኣቃዎች በጽዳት መያዝ፣ ወሲብ ሲፈጸም መከላከያ (ኮንዶም) መጠቀም ያስፈልጋል። በጣልያን ኣገር እድምያቸው ከ 12 በታች ለሆኑትን ከ 1991 ጀምሮ የግድ ክትባት ማድረግ ኣለባቸው።
ላንዳንድ ኣደገኛ በሽታ ላለባቸውና ለካምፕ ሰራተኞች ይህን ዓይነት ክትባት እንድያደርጉ ምክር ይሰጣል።

## ሂፓታይት ሲ- C

ይህን በሽታ ባለም ምሉ የሚታይና የተስፋፋ በሽታ ሆኖ መጀመርያ ላይ ብዙ ምልክት ኣያሳይም። 85% የታመሙትን ሰዎች ወደ ከፍተኛ የሀመም ደረጃ ልያደርሳቸው ይችላል።

ልክ ሂፓታይ ቢ B እንደሚተላለፍ ይህን ኣይነት በሽታ በደም ኣመካኝነት ይተላለፋል። እስካሁን ድረስ ለሂታታይት ሲ C የሚፈውስ ክትባት ኣልተገኘም። ዋናው ጥንቃቄ መሰረታዊ የንጽህና ስርዓቶች መከተል ነው።
ስደተኞችና (መኖርያ ፈቃድ ባይኖራቸውም) የዚህ ሃገር ዜጎች የምያስፈልገውና ተገቢው ህክምና ማግኘት ይችላሉ።

## ኤች ኣኢ ቪ ቫይረስ

የኤች ኣኢ ቪ ቫይረስ በደም የሚተላለፋል ሆኖ ከእናት ወደ ሽል፣ ወተት በማጥባትና ያለመከላከያ ወሲብ ሲፈጸም ይዘዋወራል። እንድያውም ምላጭ በመለዋወጥንና ያለዋስትና የሚፈጸሙትን አደገኛ ልምዶች ነው። የኤች ኣኢ ቪ ቫይረስ ምልክቶች የሚታዩትን ከተወሰኑ  ሳምንታት እስከ ሶስት ወር ብቅ ማለት ይችላሉ። ቢሆንም መታመሙን የሚጠራጠር ሰው ምልክቶቹን እስከሚታዩ ሳይጠብቅ ወደ ህክምና

መሄድ ይገባዋል። ይህን ቫይረስ መኖሩን ለማጣራት የሚደረጉትን ምርመራዎች ከክፍያ ነጻ ናቸው።
የምርመራው ውጤት ደግሞ በህግ መሰረት ለባለቤቱ ብቻ እንጂ ለሌላ ሰው መንገር ወይም መስጠት ኣይቻልም (05/06/1990 የታወጀው 135 ቁጥር ህግ)።
በጣልያን ኣገር ከእድሜ በታች የሆኑትን ይህን ምርመራ ለማድረግ የቤተሰባቸው ፈቃድ ያስፈልጋቸዋል።

### ኤች ኣኢ ቪ ቫይረስ የማይተላለፍበት መንገድ

- እጅ በመጨበጥ፣ በማቀፍ፣ ልብስ በመለዋወጥ ኣይተላለፍም
- በመሳም፣ በምራቅ፣ በመንከስ፣ በመጫር፣ በመሳል፣ በራብ፣ በእንባ፣ በሽንት ወይም ሰገራ ኣይተላለፍም
- ብርጭቆ ፣ ማንክያ፣ ሹካ፣ ሳህን፣ ሽንትቤት ውስጥ በሚገኙት መሳርያዎች፣ ኣንሶላ፣ ፎጣ በመለዋወጥ ኣይተላለፍም
- ትንኝ ሲወጋን ኣይተላለፍም

### ይህን ቫይረስ የማያስተላልፉት ቦታዎች

- ጂም ወኢም የስፖርት ኣዳራሾች፣ መዋኛ ቤቶች፣ ሽንትቤት፣ ገላ ማጠብያ ክፍል
- ትምህርት ቤት፣ መዋዕለ ሕጻናት፣ ጽህፈት ቤት
- ምግብ ቤት፣ ቡና ቤት፣ ሲኒማ ቤትና የመዝናኛ ኣዳራሾች
- መጓጓዣ( ኣውቶቡስ ታክሲ ወዘተ)

ይህን የኤች ኣይ ቪ ቫይረስ በወሲብ እንዳይተላለፍ ከማይታወቅ ሰው ጋር ወይም ኣዲስ ከሆኑት ጓደኛዎች ወሲብ ሲፈጸም መከላከያ ወይም ኮንዶም መጠቀም ይገባል። በተጨማሪም በደም እንዳይተላለፍ የተጠቀሙበት መርፍየ ከእንደገና ኣለመጠቀም ያስፈልጋል።
በጤና ማዕከላታ የሚሰሩት ሞያውያን ጓንት እየተጠቀሙ ከማንኛውም አደጋ መጠንቀቅ ያስፈልጋቸዋል።

### ሳንባ ነቀርሳን የሚመለከት መረጃ

ወደ ጣልያን ኣገር የሚመጡት ስደተኞች በግዜው ይህን በሽታ በሚመለከት ተገቢው ምርመራዎች ማድረግ ይገባቸዋል። በተጨማሪም ሃኪሞች ስለ ሳንባ ነቀርሳ መረጃና ጥያቄ ማድረግ ይገባቸዋል።

ለሁለት ሳምንት ያህል የሚቆይ ሳል ሲከሰት የሳምባ ምርመራና (ኤክስረይ) የደም ምርመራ ማዘዝ ይገባል።
ተገቢውን የጥንቃቄ ሂደቶች ከተመከረ በሃላ ደግሞ የታመመውን እስከሚድን በየግዜው ቁጥጥር እንድያደርግ ምክር መስጠት ያስፈልጋል።

**ምልክት የማያሳይ የሳንባ ነቀርሳ ብክለት ITL**

በሁለተኛ ደረጃ የስደተኞች ማጥለያ ካምፕ የሚኖሩትን በተለይ ደግሞ በስደት ጉዞኣቸው ከታመሙት ሰዎች የተቀላቀሉት እንደዛም በብዛት ሳንባ ነቀርሳ ከሚታይበት ሃገሮች ለሚመጡት ስደተኞች ምርመራ እንድያደርጉ በከፍተኛ ሁኔታ ይመከራል። ምርመራው TST ተብሎ በሚጠራ ዓይነት ምርመራ ይደረግና ውጤቱን ከታየ በሃላ ተገቢውን ህክምና ይጀመራል። _>10 ሚሊሜተር ዲያሜትር ስፋት ያለው ውጤት ሲከሰት ብክለት እንዳለ ያረጋግጣል። ይህን ዲያሜትር ክ>5 ከሆነ ብክለት እንደሌለ ያመለክታል። ሆኖም ግን ኤች ኣይ ቪ ከታመሙትን ወይም ያልተመጣጠነ ምግብ ከማያገኙትንና ሳንባ ነቀርሳ ከታመሙትን ጋር የተቀላቀሉትን ሰዎች ሲዛመድ ብክላት እንዳለ ያመለክታል።

IGRA ተብሎ የሚታወቅ ዓይነት ምርመራ የሳንባ ነቀርሳ ክትባትና TST ምርመራ ላደረጉት ነው። ዕድምያቸው ከ 15 በታች ለሆኑትን TST የተባለውን ምርመራ ብቻ ማድረግ ይገባል።

ምልክት የማያሳይ ዓይነት የሳንባ ነቀርሳ ብከላ ITL የምያሳዩት ሰዎች ልክ እንደታመሙትን ሰዎች ተገቢው ክትትል ማድረግ ይገባቸዋል።

**ክትባት**

ከአዕድሜ በታችና እስከ 18 እድሜ ያሉትን

- ክትባት ያልተከተለ ህጻን ያላደረገውን ክትባት ምድረግ ይገባዋል
- በኣገር ቤት ሁሉም የሚገባውን ክትባት ያሟላ ማስረጃ ወረቀት ኣሳይቶ ቀሪው

ክትባት ያደርጋል
- ከኣገር ቤት የሚቀርቡት መረጃ ወረቀቶች ኣጠራጣሪ ወይም ግልጽ ካልሆኑት ልክ እንዳልተከተበ ተቆጥሮ ክትባቱን ከእንደገና ይጀምረዋል

**ከ 18 እድሜ በላይ ለሆኑትን**

በህግ መሰረት የሕክምና ማዕከላቶች ጸረ ቲታነስ፣ ጸረ ፖልዮ፣ ጸረ ኩፍኝ፣ ለጆሮ ደገፍና የጀርመን ኩፍኝ  የሚከላከል የግዴታ ክትባት ናቸው

እላይ ከተዘረዘሩት ክታበቶች ጭምር የሚቀጥልቱን እንዲደረጉ (LG ) ተብሎ የሚታወቅ የድንበር የጤና ዋስትና ቁጥጥር ይመክራል

- ጸረ ፖልዮ፣ ጸረ ዲፍተርያ፣ ጸረ ቲታነስ፣ ጸረ ትክትክ ሳል
- ጸረ ኩፍኝ፣ ጸረ ጆሮ ደገፍ፣ ጸረ ጀርመን ኩፍኝ፣ ጸረ ፈንጣጣ (ነፍሰ ጡር ሴት ኣይመለከትም)
- ጸረ ሂፓታይት ቢ B እድምያቸው ከ 18 በላይ ለሆኑትን ይመለከታል

ይህን ሁሉ የተዘረዘሩትን የክትባት ዓይነት (ከሂፓታይት ቢ B በስተቀር) ያለ ኣስፈላጊነት ማድረግ ኣይገባም። ሁሉንም የተደረገውና ገና ቀሪ የሆኑትን ክትባቶች በክትባት ደብተር መጻፍ ኣለባቸው።

**<u>የማህጸን ህክምና</u>**
ለሴት ልጅ ጤና ብሎ የተመሰረተው የጤና ማእከል ኮንሱልቶርዮ (consultorio) ተብሎ ይጠራና ከታች የተዘረዘረው ኣገልግሎት ይሰጣል።
**የማህጸን ህክምና፣** ባለሞያ ሃኪም የማህጸን ህክምናና ከሱ ጋር የተያያዙት ጥቆማዎች ይሰጣል። ይህን ኣይነት ምርመራ በኣመት ኣንዴ እንዲደረግ ምክር ይሰጣል።
**<u>ፓፕ ተስት (pap test) ፣</u>** ማህጸን ውስጥ የሚገኙትን ህዋሳት በማጥናት የሚካሄድ ምርመራ ሆኖ በማይክሮስኮፕ ተመርምሮ የነቀርሳ ወይም የካንሰር ምልክት መኖር ኣለመኖር ያሳያል። እድሚያቸው ከ 25 በላይ የሆኑትን ሴቶች በየሁለት ኣመት እንድያደረጉ ምክር ይሰጣል።
**<u>የጡት ኤክስረይ ወይ በጨረርታ የሚነሳ ፎቶ፣</u>** ጡት ውስጥ የነቀርሳ ወይም የካንሰር ምልክት መኖር ኣለመኖር የምያሳይ ምርመራ ሆኖ እድሚያቸው ከ 40 በላይ

ለሆኑትን በ 18 ወር እንድያደረጉ ምክር ይሰጣል።

**<u>የመውለድ ግዜ ሲቀርብ የሚደረግ ምርመራ (ኣዋላጅ)፣</u>** ይህን ምርመራ የእናትና ማህጸን ላይ ያለ ልጅዋን የጤናቸው ሁኔታ የሚከታተል ምርመራ ሆኖ 30/40 ባለው ግዜ ውስጥ ማድረግ ይገባል። በተጨማሪም በወር ኣንዴ የደም ምርመራና በየ ሶስት ወር የልጁን ሁኔታ የሚከታተ ኤክስረይ መነሳት ያስፈልጋል።

**<u>የመውለድ ዝግጅት፣</u>** የመውለድ ዝግጅት ለሚመለከት የልምምድ ትምህርት ላይ መካፈል ይቻላል። ይህን ኮርስ ከማህጸን ሃኪም፣ ካዋላጅ፣ ከህጻን ሃኪም በመተባበር ይካሄዳል። ሳሚፎ (Sa.Mi.Fo) ጤና ማእከል ውስጥ እንደዛም በ Asl Roma1 ይህን የተጠቀሰው ኮርስ በሴቶች ተርጓሚ ኣመካኝነት ይካሄዳል።

**<u>የኣእምሮ ህክምና</u>**

ለሰው ልጅ ዋናውና ከፍተኛ ጤና የኣእምሮ ጤና ነው።

በሂወታቸውና በስደት ጉዞኣቸው መጥፎና ኣስቀያሚ ግዜ ያሳለፉትን ሁሉ በቀላሉ የኣእምሮ ችግር ተጠቂዎች መሆን ይችላሉ።

የተረበሸ እንቅልፍ የሚተኙ፣ በቀላሉ ኣንባቸው የሚፈስ፣ ኣሳዛኝ ትዝታ የሚመጣባቸው ፣ ብቸኛ መሆን የሚፈልጉት፣ ብዙ ሰው ከሚሰበሰብበት በታ መራቅ፣ የማስታወል ችሎታ ሲቀንስ፣ የኣካል ህመም፣ ያልተለመደ ጸባይ፣ የጫስ ሱሰኛ መሆን የመሳሰሉትን ምልክቶች ብቅ ሲሉ በግል ወይም በስደተኞች መጥለያ በሚሰሩት ኣመካኝነት ወደሚመለከተው የህክምና ባለሞያ መምራት ያስፈልጋል። የታመሙትን ስደተኞች በመጀመርያ ለግል ሃኪማቸው ኣሳውቀው በሚኖሩበት ኣከባቢ ወደሚገኝ የኣእምሮ ህክምና ማእከል በመሄድ ()የሚገባውን ውይይትና ህክምና ማግኘት ይቻላል። ኣስቸኳይ ሁኔታ በሚከሰትበት ግዜ 118 በመደወል እርዳታ መጠየቅ ይቻላል። በጣም ከባድ የኣእምሮ በሽተኞች መታከም እምቢ ካሉ 118 በመደወል ቲ ኤስ ኦ (T.S.O)የሚባለው ኣገልግሎት መጥራት ይቻላል። ይህን ኣይነት ኣገልግሎት ማንኛውም ሰው መጥራት ቢችልም ታካሚው ሆስፒታል መተኛት እንዳለበት የሚወስኑት የዚህ ኣገልግሎት ኣባላቶች ብቻ ናቸው።

## በስደተኞች ማጥለያ ካምፕ ለሚሰሩትን የሚመለከት የስራ ዋስትና (ምያዝያ 9 2008 ህግ ዓንቀጽ 81)

ዓንቀጽ 6 መሰረት በማድረግ የውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር እንዳወጀው በስደተኞች ማጥለያ ካምፕ ለሚሰሩትን የሚመለከት የስራ ዋስትና

የካቲት 25 2005 የተሰራጨውና(ግንቦት 11 2005 የጸደቀው የውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር መምርያ ስራ ቦታ ድህንነትና ዋስትና እንዲኖር ይከታተላል። ቀጥሎ መስከረም 19 1994 የታወጀውን ህግ እላይ የተጠቀሰውን ህግ ኣንዳንድ ለውጦች ይጨምራል። ይህን የመጨረሻ መምርያ በመጥለያ ካምፖች ውስጥ የመጀመሪያ እርዳታና የቃጠሎ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን እንዲመረትጥ ይወስናል።
ማጋቢት 20 2014 የወጣውን 2204 ቁጥር መምርያ ለስደተኞች ማጥለያ ቦታ እንዲገኝ መምርያ የሚሰጥ ኣዋጅ ነው።

**ዓንቀጽ 10**
ህጉን ላይ እንደጠቀሰው መጥለያ ካምፖች ተገቢው ዋስትና እንዲከታተሉ፣ ጽዳት እንዲጠብቁና ቃጠሎ ሲነሳ ለማጥፋቱ የምያስፈልጉትን መሳርያዎች እንዲኖሩት የምያስታውስ ህግ ነው። (ምያዝያ 9 2008 የወጣው ህግ ቁጥር 81 )
ከተጠቀሰውን ህግ ጎን ለጎን የሚሄደውን በውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር (መጋቢት 7 2017 ቁጥር 3594) የታወጀው ህግ ይገኛል።

## ዓንቀጽ 4 - ስራ ቦታ ውስጥ መከተል የሚገባው የጤናና ደህንነት ዘዴ

ምያዝያ 9 2008 ቁጥር 81 የወጣ ህግ ስራ ቦታዎች ተገቢው ዋስትና እንዲኖራቸው የምያስታውስ ኣዋጅ ሆኖ ስለ መጀመርያ እርዳታና ስለ ቃጠሎ ማስታወሻና መምርያ ይሰጣል።

## የኤውርፓ ማህበር ኣባላት U.E ላልሆኑት ስደተኞች የሚመለከት የህግ ኣርእስታቶች

- መጋቢት 6 1998 ቁጥር 40 ህግ ቱርኮ ናፖሊታኖ በሚል ስም የሚታወቀው (ኣንቀጾች 32, 33, 34)

- ሃምሌ 25 1998 ቁጥር 286 ህግ የስደተኞች ኣስተዳደር የሚመለከትና(ኣንቀጾች 34, 35, 36) ቀጥሎ የተደረገውን የህጉን ማሻሻል (ኣንቀጾች 42, 43, 44)

- መጋቢት 24 2000 ቁጥር 5 የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ያወጣው የህጎች ተግባራዊነት የሚከታተል ኣዋጅ

- ታህሳስ 20 2012 ቁጥር 255 የወጣው በመንግትና ኣውራጃዎች የተፈረመውን ዉል የስደተኞችን የህክምና ማግኘት መሰል የሚከታተል ህግ ነው

- ነሃሴ 18 2015 ቁጥር 18 የወጣው ኣዋጅ የ 2013/33/U.E መምርያ ማለት የፖለቲካ ጥገኝነ ጠያቂዎች መሰል ተግባራዊ እንዲሆን የሚከታተል ነው። በተጨማሪም ፖለቲካ ጥገኝነት ስለ መስጠትና መንፈግ የሚከታተል መምርያ 2013/32/U.E (ኣንቀጽ 21)

## ከዕድሜ በታች ለሆኑት ስደተኞች የሚመለከቱ የህግ ኣርእስታቶች

- ህዳር 10 2016 ቁጥር 234 የወጣ ኣዋጅ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ስለ ሞግዚት የሌላቸው ከዕድሜ በታች ነን ለሚሉትን ሃቅ መሆኑን ለማጣራት የወጣ ኣዋጅ (መጋቢት 4 2014 ቁጥር 2 ፣ የህግ አንቀጽ 4፣ ንኡስ አንቀጽ 2)

- ሰኔ 12 2017 የሚኒስትሮች ምክር ቤት ስለ ማህበራዊ ኣገልግሎት (የህግ አንቀጽ 1፣ ንኡስ አንቀጽ 7 ታህሳስ 30 1992 ቁጥር 502) ህጋዊ መኖርያ ፈቃድ ለሌላቸው ከዕድሜ በታች ለሆኑት ስደተኞች የህክምና መሰላቸው የሚጠብቅ ኣዋጅ ነው።(የህግ አንቀጽ 3፣ ንኡስ አንቀጽ 4)

በተጨማሪም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ (234/2016) እንደዛም (7/2017 ህግ)ከዕድሜ በታች ለሆኑት የሚመለከት ስለመሰላቸው በኣጠቃላይ ይከታተላል። (16/30/CR 09/C7-C15) መጋቢት 3 2016

## ክትባት የሚመለከቱትን የህግ ኣርእስታቶች

- ብሄራዊ የክትባት ስርጭት የሚመለከት 2017-2019 ቁጥር 10/CSR 17A01195, GU. የካቲት 18 2017 ቁጥር 41 ህግ
- መጋቢት 16 2017 ቁጥር 0089 ኣንቀጽ 8 ንኡስ ኣንቀጽ 6 መሰረት በማድረግ ሰኔ 5 2003 ቁጥር 131 የታወጀውን በመንግስትና በትረንቶና በልዛኖ ኣውራጃዎች መካከል ብሄራዊ የክትባት ስርጭት የሚመለከት ኣዋጅ 2017-2019 (10 CSR 19/01/2017)

- ሰኔ 7 2017 ቁጥር 73 የታወጅውን ክትባት የሚመለከቱትን የህግ ኣርእስታቶች

- ሃምሌ 31 2017 ቁጥር 119 የታወጅውን ሰኔ 7 2017 ቁጥር 73  የተወሰነውን እርማት የሚጨምር (ነሃሴ 5 2017 ቁጥር 182)
- ነሃሴ 14 2017 ቁጥር 252146 በጤና ሚኒስቴር የታወጀውን ከስር ለተጠቅቀሰውን እርማት ተግባራዊ የምያደርግ ህግ( ክትባት፣ ተላላፊ በሽታዎች፣ ማከም)
- 18/08/2017 ቁጥር 25233 በጤና ሚኒስቴር የታወጀውን በግዝያቸው ላልተከተቡትን ከዕድሜ በታች ለሆኑትን የሚመለከት
- 15/01/2018 ቁጥር 1174 በጤና ሚኒስቴር የታወጀውን ከሰሜን ኣፍሪቃ በብዛት ከሚመጡትን ስደተኞች የፖሊቫኢረስ መስፋፋት የሚመለከትና ለሱ የሚሆን ክትባት መስጠት የሚመለከት የህግ ኣርእስት
- ከሚኒስቴር የተሰራጨው የ 09/05/2014 ቁትር 12942 መምርያ ከዕድሜ በታች ለሆኑትን ስለሚሰጥ የክትባት ደብተር የሚመለከት
- 23/03/1993 ቁጥር 8 በጤና ሚኒስቴር የታወጀውን ስደተኞች በብዛት በሚመጡት ግዜ የፖሊቫይረስ መስፋፋትና የሚከታተል ህግ
- 29/05/2017 ቁጥር 18366 በጤና ሚኒስቴር የታወጀውን  ከላይ ለተጠቀሰውን ህግ ( በ 29/05/2017 ቁጥር 0016664)ስለ ፖሊቫይረስና ለሱ የሚሆን ክትባት እርማት የሚጨምር ህግ
- 23/03/2011 የጸደቀው በመንግስትና ኣውራጃዎች መካከል የተፈረመውን ስለ ኩፍኝና የጀርመን ኩፍኝ 2010-2015 ብሄራዊ የክትባት ስርጭት

## ተጨማሪ ማጣቀሻ ሰነዶች

በኣውራጃዎችና ወረዳዎች የተፈረመው ተዳዳሪ ያልሆኑ ታዳጊዎች የሚመለከት ውል 16/30/Cr09/C7-C15
http://www.minori.gov.it/sites/default/files/protocollo_identificazione_msna.pdf

በ 31/08/2016 በፕረዚደንት የተፈረመውን ታዳጊዎች የምያስፈልጋቸው ክትትል የሚመለከት  2016/2017 ቁጥር 267 እና 15/11/2016 ቁጥር 50 የታወጀው
http://www.gazzettaufficiale.it/eli/gu/2016/11/15/267/so/50/sg/pdf

03/04/2017 በጤና ሚኒስቴር የታወጀውን ስለ መሰረታዊና ስነኣምሮኣዊ ህክምና የሚመለከት ሆኖ ልዩ ዓይነት ግፍ፣ ድፍረት ላጋጠማቸው፣ ስነኣምሮኣዊ በደል

ለደረሰባቸው የሚመለከት 24/04/2017 ቁጥር 95 የታወጀ ህግ ነው።
30/03/2017 የተፈረመው ቁጥር 43 በመንግስትና ኣውራጃዎች የተፈረመ ውል ነው።
http://www.salute.gov.it/mgs/C_17_pubblicazioni_2599_allegato.pdf

ስደትና ጤና ተብሎ የሚጠራ 23/06/2017 የቆመ ብሄራዊ ድርጅት
http://bioetica.governo.it/media/172302/p128_2017_immigrazione-e-salute_it.pdf

21/01/2014 ቁጥር 18 የውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር ፖለቲካዊ ጥገኝነት የተሰጣቸው ስደተኞች በማህበራዊ ሂወት ማሳተፍ ያቀደ ህግ ነው
http://www.interno.gov.it/sites/default/files/piano-nazionale-integrazione.pdf

INMP, ISS, SIMM ልክ የጣልያን ድምበር ተሻግረው ወደዚህ ሃገር ለገቡትና መጥለያ ካምፕ እንደደረሱት የሚሰጥ የጤና እርዳታ ሰኔ 2017 (isbn 9788898544189)።
በመንግስትና ኣውራጃዎች የተፈረመ ውል 10/05/2018 ቁጥር 108።
http://www.simmweb.it/920-accordo-stato-regioni-lg-accoglienza

ማህመር ፓርሰክ፣ ሚላኖ የሚገኝ ፐቢኮካ ዩኒቨርሲቲ፣ ሳን ካሚሎ ፎርላኒኒ፣ ኖሶትሮስ፣ ትራማ ዲ ተራ የሚባለው ማህበር ስለ ሴት ልጅ ግርዛትና ሌላ መጥፎ ባህላዊ ልምምዶች የሚመለከት 2018
http://www.simmweb.it/attachments/article/909/riconoscimento_precoce_vittime_MGF.pdf

INMPS, ISS, SIMM በስደተኞች መካከል የሳምባ ነቀርሳ ስርጭት ቁጥጥር ለካቲት 2018
http://www.inmp.it/lg/LG_Tubercolosi.pdf

የፓርላማ ኮሚሽን ስለ ስደተኞች ኣቀባበል፣ ፖለቲቻዊ ጥገኘነት ኣሰጣጥና ወደ ኣገራቸው መመለስ
http://www.interno.gov.it/sites/default/files/allegati/relazione_commissione_tutela_salute_migranti_e_popolazione_residente.pdf

**ወደ ብሄራዊ የጤና አገልግሎት ለመካፈል የሚረዱት መምርያዎችና ጥቆማዎች**

| ኣዋጅ | ኣዋጁን የሚመለከተው ጉዳይ | ኣዋጁን የሚመለከተው ሰው/ተጠቃሚ |
|---|---|---|
| 25/08/98 የዋጣ ኣዋጅ ቁጥር 286 ኣንቀጽ 34 ስደተኞችን የሚመለከት | ወደ ብሄራዊ የጤና አገልግሎት የግዴታ ምዝገባ | ጣልያን ኣገር ውስጥ ህጋዊ መኖርያ ፈቃድ ይዘዉ ለሚኖሩት ስደተኞች፣ ፖለቲካ ጥገኝነት ላገኙት፣ ኡማኒታርያ፣ ሱሲድያርያ የሆነውን መኖርያ ፈቃድ ላላቸው ይመለከታል |
| በመንግስትና፣ ኣውራጃዎችና ወረዳዎች የተፈረመ ህግ 20/12/2012 ቁጥር 225 | ወደ ብሄራዊ የጤና አገልግሎት የግዴታ ምዝገባ | ኣንቀጽ 34 ንኡስ ኣንቀጽ 1 መሰረት በማድረግ<br>• ፖለቲካ ጥገኝነት ያገኙት<br>• ኡማኒታርያ ወይም ሱሲድያርያ መኖርያ ፈቃድ ላላቸው<br>• የፖለቲካ ጥገኝነት ጠያቂዎች<br>• የፖለቲካ ጥገኝነት ጠያቂዎች (የዱብሊን ስምምነት)<br>የመኖርያ ፈቅድ ጠይቀው ገና ተጠባባቂ ለሆኑትን ጤና ኣገልግሎት እንድያገኙ በህግ መሰረት ይፈቀድላቸዋል |
| 24/03/2000 በጤና ሚኒስቴር የታወጀው ፖለቲካ ጥገኝነት የተሰጣቸዉ፣ ኡማኒታሪና | ወደ ብሄራዊ የጤና አገልግሎት የግዴታ ምዝገባ | ፖለቲካ ጥገኝነት ያገኙት፣ ኡማኒታርያ፣ ሱሲድያርያ የሆነውን መኖርያ ፈቃድ ላላቸው፣ ፖለቲካ ጥገኝነት ጠያቂዎች ለሆኑትና እንደዘም ይግባኝ ብለው |

| | | |
|---|---|---|
| ሱሲድያርያ ተብሎ የሚጠራው መኖርያ ፈቃድል ላገኙት፣ ፖለቲካ ጥገኝነት ጠያቂዎች ለሆኑትና ይግባኝ ላሉትን የሚመለከት ኣዋጅ | | የፍርድቤት ውሳኔ ለሚጠብቁት የሚመለከት ኣዋጅ ነው |
| 18/08/15 የዋጣ ኣዋጅ 142 ቁጥር 21 | ኣንቀጽ 34 መሰረት በማድረግ የፖለቲካ ጥገኝነት ጠያቂዎች የሆኑት ወደ ብሄራዊ የጤና አገልግሎት መመዝገብ እንዳለባቸው የሚወስን መምርያ | የፖለቲካ ጥገኝነት ጠያቂዎች ለሆኑት የሚመለከት |
| 25/07/98 የዋጣ ኣዋጅ ቁጥር 286 ኣንቀጽ 35 በኣውራጃዎችና ወረዳዎች የተፈረመ ውል 225/CSR 20/12/2012 | **STP ጣልያን ኣገር ውስጥ ያለህጋዊ መኖርያ ፈቃድ ለሚኖሩት ስደተኞች የሚሰጥ የህክምና ወረቀት ሆኖ በተለያዩት የጤና ኣገልግሎት እንዲካፈሉ ይፈቅዳል።**<br>• ነፍሰጡርና ለወለዱት እናቶች የሚመለከት ኣዋጅ ቁጥር 405 29/07/1975 - ኣዋጅ ቁጥር 194 22/05/1978። በተጨማሪም በ 06/03/1995 የጤና ሚኒስቴርና እንዳወጀውና በ 13/04/1975 በጋዜጣ እንደተሰራጨው<br>• ከእድሜ በታች ለሆኑትን የጤናና የህክምና መሰላቸው የሚመለከት 20/11/1989<br>• ህግን በመከተል የክትባት ግዜ መከታተል<br>• ተነቃፊ ህመሞች የሚመለከት ክትባት | ጣልያን ኣገር ውስጥ ያለህጋዊ መኖርያ ፈቃድ የሚኖሩት ስደተኞች STP በመጠቀም ይታከማሉ |

| | | |
|---|---|---|
| | • ክትባትና ከሱ ጋር የተያያዘ ህክምና<br>• የኣደንዛዥ ዕጸ ሱሰኞች ተጠቃሚ ለሆኑትን የሚመለከት | |